በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
ለኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን
አዲስ አበባ

ጉዳዩ:- የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱን ከየካቲት 1 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ ያለው ሂሣብ ኦዲት የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት ይመለከታል፤

በርዕሱ የተጠቀሰው ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት ከየካቲት 1 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ ያለው_ሂሣብ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦችን የያዘ 13 ገጽ የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት (Final Management Letter) እና 1 ገጽ አባሪ በድምሩ 14 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን ልከናል። በመሆኑም በገጽ 15 በተመለከተው የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርዓ-ግብር ቅጽ መሰረት የተወሰዱ እርምጃዎች በአስቸኳይ እንዲላክልን እናሳስባለን።

ከሰላምታ ጋር !

ሰለሞን መብራቱ
የልማትና ማኅበራዊ መሥሪያ ቤቶች
ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# በእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር

# የኢትዮጲያ ሆርቲካልቸርና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን

ከየካቲት 1 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ

ያለው ሂሣብ ኦዲት የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት

**መጋቢት 2010 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ**
**የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን**
**ከየካቲት 1 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ**
**ያለው ሂሣብ ኦዲት የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት**

## መግቢያ

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመሥሪያ ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የኢትዮጲያ ሆርቲካልቸርና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ከየካቲት 1 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ ባለው ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለን ዘንድ ሂሳቡን ኦዲት አድርገናል።

## ዓላማ

የዚህ ደብዳቤ ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶችን የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱበት ለማድረግ ነው።

## የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው የዓለም አቀፍ የመንግሥት ኦዲት ደረጃዎችን (INTOSAI/ISA) መሰረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው። እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ (የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል።

## ኦዲታችን የሚያካትተው፡-

- ✓ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና መመርመርን፣
- ✓ የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- ✓ የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ለፌዴራል መንግሥት አጠቃላይ ዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ ዝግጅት አግባብነት ያላቸው መሆኑን፣ ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል።

ከዚህም በተጨማሪ የሂሳብ መግለጫዎቹ ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና መመርመርን ይጨምራል።

የሂሳብ መግለጫዎቹ ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆናቸው በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል። አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል።

በመሆኑም በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት የአሰራርም ሆነ የሂሳብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሳብ መግለጫውን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም።

የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ከዚህ ጋር የተያያዙ ግድፈቶችና ስህተቶች ሁሉ ሊታወቁ የሚችሉት ይህን አስመልክቶ ሰፊ ጊዜ በመውሰድ ልዩ የዝርዝር ኦዲት በጥልቀት ሲከናወን መሆኑን እንገልጻለን።

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ኃላፊነት ነው።

## የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ሥራ አመራር ከየካቲት 1 ቀን 2009 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ ባለው ሂሣብ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ረቂቅ ሪፖርት ላይ ምላሽ እንዲሰጥ የካቲት 22 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር OFAGF-02.5/7/10 በተጻፈለት ደብዳቤ መሰረት ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ መጋቢት 5 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር 18/በ80/01/11/203 በተጻፈ ደብዳቤ ምላሽ ሰጥቷል። በመሆኑም ለሥራ አመራሩ የተዘጋጀው የመጨረሻው ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 1. የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት

#### 1.1. መሥሪያ ቤቱ በህግ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ያለው የሂሳብ ምዝገባ እና የሂሳብ ሪፖርት ተለይቶ እንዲዘጋጅ ያልተደረገ ስለመሆኑ፤

##### 1.1.1. ግኝት

የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 152/2000 እንዲሁም የኢትዮጵያ ግብርና ኢንቨስትመንት መሬት አስተዳደር ኤጀንሲ በሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር 283/2003 ተቋቁመው የነበሩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የነበሩ ሲሆን ከታህሳስ 21 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ ሁለቱ መሥሪያ ቤቶች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 396/2009 ተዋህደው የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን በሚል ስያሜ መቋቋሙን መገንዘብ ተችሏል። በመሆኑም ሁለቱ ኤጀንሲዎች የተቋቋሙበት ደንብ እስከተሻረበትና እስከተዋሃዱበት ጊዜ ድረስ ያለው ሂሳባቸውን መዝግበው ለገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር ሪፖርት አቅርበዋል። ሆኖም ሁለቱ አጀንሲዎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ከተዋሃዱበት ጊዜ ጀምሮ ያለው በተናጥል የሰሩት ሂሳብ ተዘግቶ እና ከሂሳብ መዝጊያ በኋላ ያለውን የሂሳብ ሚዛን (Post Closing Trial Balance) ተዘጋጅቶ አዲስ ለተቋቋመው ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት የመነሻ ሂሳብ አድርጎ በመነሳትና የቀጣይ ወራቶችን ምዝገባ በማከናወን የሂሳብ ሪፖርት ማዘጋጀት ሲገባ የባለሥልጣን መሥሪያ ቤት የሂሳብ ምዝገባና የሂሳብ ሪፖርት እንዲዘጋጅ የተደረገው፡-

1. የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ እስከ የካቲት 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ ያለው ሂሳብ ከላይ በተገለጸው አግባብ ተዘግቶና ከሂሳብ መዝጊያ በኋላ ያለው የሂሳብ ሚዛን (Post Closing Trial Balance) ተዘጋጅቶ ከመጋቢት 1 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ተዋሃደው ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት እንዲዞር ተደርጓል።

2. የኢትዮጵያ ግብርና ኢንቨስትመንት መሬት አስተዳደር ኤጀንሲ ሂሳብ ግን ሂሳቡ ተዘግቶ ወደ የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን እንዲዞር ሳይደረግ ኤጀንሲው ከሐምሌ 1 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ ባከናወነው የሂሳብ ምዝገባ ላይ እንዲቀጥል በመደረጉ ምክንያት ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ሂሳብ ተለይቶ የሂሳብ ሪፖርቱም በዚሁ አግባብ ባለመቅረቡ ምክንያት የተዘጋጀውን የሂሳብ ሪፖርት አግባብነት ለማረጋገጥ አልተቻለም።

**1.1.2. <u>ሥጋት</u>**

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 396/2009 የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ያለው የሂሳብ ሪፖርት ተለይቶ ካልቀረበ በተዘጋጀው የሂሳብ ሪፖርት ላይ አስተያየት ላይሰጥ ይችላል፡፡

**1.1.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>**

የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየት ለመሰጠት ይቻል ዘንድ ከላይ በግኝቱ ላይ በተቀመጠው አግባብ ሂሳቡን በመለየት የሂሳብ ሪፖርቱን ለኦዲት ዝግጁ ማድረግ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን።

**1.1.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>**

ሚያዝያ 24 ቀን 2009 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 18/በ07/1/08/160 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በተጻፈ ደብዳቤ ሁለቱን ኤጀንሲዎች እንዴት ማዋሃድ እንዳለብን ማብራሪያ የጠየቅን ሲሆን፣ ግንቦት 1 ቀን 2009 ዓ.ም

ከገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር በቁጥር ክሂሐጊ/74/ በተጻፈ ደብዳቤ በተሠጠን ማብራሪያ፡-

1. በአዲሱ አደረጃጀት ለመሥሪያ ቤቱ የተሰጠ መለያ ቁጥር 215 በመሆኑ ይህንን መለያ ቁጥር ይጠቀም የነበረው ተቋም ሂሣብም እንደነበረ የሚቀጥል መሆኑ፣

2. ቀደም ሲል መለያ ቁጥር 218 ይጠቀም የነበረው የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲን በተመለከተ የመጨረሻው ወር ሂሣብ ሪፖርት ከወጪ ቀሪ ላይ የሚታየው ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሣብን በሙሉ የተጣራ ሃብትን በመንካት ማጥፋት እንዳለብን፣

3. በሌላ በኩል ከመለያ ቁጥር 215 ወደ መለያ ቁጥር 218 የተላለፈውን ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሣብ የተጣራ ሀብትን በመንካት ሂሣቡን እንደምንመዘግብ፣

4. ከዚህ ጋር በተያያዘ ለሁሉም ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሣቦች በዝርዝር የተቀጽላ ሌጀር ሊከፈትላቸው እንደሚገባ፣

5. ቀደም ሲል በመለያ ቁጥር 218 ኮድ በሆርካልቸር ልማት ኤጀንሲ ስም ተከፍተው የነበሩ የባንክ ሂሣቦች አካውንት በሙሉ ተዘግተው በባንክ እና በሳጥን ያለው ጥሬ ገንዘብ የተጣራ ሀብትን (5601) በመንካት ወደ መለያ ቁጥር 215 ሊዞር እንደሚገባ፣

ተገልጾ በተሰጠን ማብራሪያ መሠረት ሁሉንም በማድረግ የሆርቲካልቸር ኤጀንሲ መለያ ቁጥር 218 ኮድ የነበረውን ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሣብ ተቀጽላ ሌጀር በመክፈት ሌሎቹን በመዝጋት ወደ አዲሱ ባለሥልጣን የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና የግብርና ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን መለያ ቁጥር 215 ኮድ ላይ አዙረን የኢትዮጵያ ግብርና ኢንቨስትመንት ኤጀንሲን እስከ መጋቢት 2009 በጀት ዓመት ድረስ የነበረው የሒሳብ ሪፖርት በተጠየቅነው መሠረት ካሣወቅን ሁለቱን ወደ አንድ በማምጣት የቀጠልን መሆኑን እንገልጻለን።

#### 1.1.5. የኦዲተሩ አስተያየት

ጉዳዩ የመለያ ቁጥር ጉዳይ አይደለም። የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ እና የኢትዮጵያ ግብርና ኢንቨስትመንት መሬት አስተዳደር ኤጀንሲ ተብለው ይጠሩ የነበሩት በሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር 396/2009 የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸርና ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ተብለው በአዲስ መልክ ተቋቁመዋል። ስለዚህ የሁለቱም የቀድሞ ኤጀንሲዎች ሂሳብ ተዘግቶ ቋሚ ሂሳቦቹ ለአዲሱ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት መነሻ ሂሳብ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል። ስለሆነ ሂሳቡ በተገለጸው አግባብ ተስተካክሎ መቅረብ ይኖርበታል። ይህ የማይሆን ከሆነ ግን በሂሳቡ ላይ አስተያየት መስጠት አይቻልም።

## 2. ተሰብሳቢ ሂሳብ

### 2.1. በደንብና በመመሪያው መሰረት ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሣብ፤

#### 2.1.1. ግኝት

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ፤ በመመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለሥራ ማስኬጃ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያመለክታል። ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ በደንቡና በመመሪያው መሰረት የፈጸመ መሆኑ ሲጣራ በ4201 ብር 50,257.81 እና 4274 ብር 30,782.24 በድምሩ ብር 81,040.05 ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ድረስ ሳይወራረድ (ሳይሰበሰብ) የቆየ መሆኑ ታውቋል።

#### 2.1.2. ሥጋት

በተሰብሳቢ ሂሳቦች ላይ ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል ካልተደረገ፡-

- ገንዘቡ ሳይሰበሰብ ሊባክን ይችላል።
- ገንዘቡ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ አይቻልም።

### 2.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት እንዲወራረዱ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

### 2.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

መመሪያው እንደተጠበቀ ሆኖ የመሥቤቱ ባህርይ ሆኖ ወደፊልድ ለረጅም ጊዜ የሚቆዩበት ሁኔታ ይታያል፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ አስተያየቱን ተቀብለን በ4201 ላይ የተያዘው በፊት ሆርቲካልቸር ኤጀንሲ የነበረው ሁለቱ መሥሪያ ቤቶች ሲዋሃዱ ወደ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት የዞረ ሲሆን በተቀጽላ ሌጀር ላይ የተያዘው ሲወራረድ በ4274 ላይ የተመዘገበ አለ እሱን አጣርተን ያልተወራረዱትን አወራርደን ማስተካከያ በመሥራት እናሳውቃለን፡፡ በ4274 ላይ የተያዙት ተሰብሳቢ ሂሣቦች የተወራዱ ሲሆን ሳይወራረዱ የቀሩት፡-

1. አቶ ጴጥሮስ ብር 3,179.50 ተሰብሳቢ ሂሣብ ሳይወራረድ ወደ ውጭ ሀገር መሄዱን
2. አቶ አስታወሰኝ ሙላት ብር 5,349.95 የሚፈለግባቸው ሲሆን ከባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ጋር በቅንጅት የመስክ ስራ በመሄድ ላይ እያሉ የመስክ ስራውን አቋርጠው በመመለስ ሂሣብ ሲያወራርዱ ያልሰሩበትን ገንዘብ እንዲመልሱ ስንጠይቅ ከደሞዛቸው እንዲቆረጥ ለፌደራል ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴሮች እንዲጻፍላቸው በጠየቁት መሰረት ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የካቲት 22 ቀን 2006 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር 18/በ07/1/07/127 በተጻፈ ደብዳቤ ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ያሳወቅን መሆኑን እየገለጽን የፌደራል ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴሮች ጠይቀን ከደመወዙ ሳይቆርጡ ኪሊራንስ እንደሰጡት ደርሰንበታል፡፡ ይሁንና ከነሱ ጋር በመነጋገር የሄደበት መሥሪያ ቤት ከደመወዙ ተቆርጦ ለመንግሥት ገቢ እንዲያደርግ እንነጋገራለን፡፡
3. አቶ ንጋቱ ቶሩ የሚፈለግባቸውን ብር 1,900.40 በአሁኑ ሰዓት በየወሩ ገቢ እያደረጉ መሆኑን እየገለጽን አጠቃላይ ያሉትን ሂሣቦች

አጣርተን የደረስንበትን ወደፊት እናሳውቃለን። ተሰብሳቢ ሂሣቦቹም ከበጀት ዓመቱ እንዳያልፉ እናደርጋለን።

#### 2.1.5. <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

- ✓ የፌዴራል ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከግለሰቡ ላይ እንዲሰበሰብ በደብዳቤ የተገለጸለት ቢሆንም ገንዘቡ እንዲሰበሰብ አልተደረገም። ስለሆነም ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ግለሰቡን በህግ አግባብ ጠይቆ ገንዘቡ ተመላሽ ማስደረግ እንዳለበት፤
- ✓ መወራረድ (መሰብሰብ) የሚችሉት ተሰብሳቢ ሂሳቦች እንዲወራረዱ (እንዲሰበሰቡ)፤ ሊወራረዱ (ሊሰበሰቡ) የማይችሉ ከሆነ ደግሞ ሁኔታው ተጣርቶ ደንብና መመሪያውን ተከትለው እንዲሰረዙ እንዲደረግ፤

እየገለጽን ለወደፊቱ በበጀት ዓመቱ የተሰጡ የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች በበጀት ዓመቱ እንዲወራረዱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል። ተወራርደዋል የተባሉት ሂሳቦች አግባብነትና ትክክለኛነት በቀጣይ ኦዲት ወቅት የሚረጋገጡ ይሆናል።

# 3. <u>ተከፋይ ሂሳብ</u>

## 3.1. <u>በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ</u>፤

### 3.1.1. <u>ግኝት</u>

በባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የሚገኙት ተከፋይ ሂሳቦችን ተገቢነት ለማረጋገጥ እንዲሁም መሥሪያ ቤቱ ያለበትን ተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል የሚከፍል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ሲደረግ በ5054 የሂሳብ መደብ 509,910.52 እና በ5061 የሂሳብ መደብ ብር 14,529.26 ከ2005 በጀት ዓመት ጀምሮ በተከፋይ ሂሳብ ተይዞ የሚገኝና ሳይከፈል ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ድረስ የቆየ በድምሩ ብር 524,439.78 የሚገኝ መሆኑ ታውቋል።

### 3.1.2. ሥጋት

የተከፋይ ሂሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ካልተወሰደ የሂሳብ ሪፖርቱን ተአማኒነት ሊያሳጣው ይችላል፡፡

### 3.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የተከፋይ ሂሳቡን ሁኔታ ተጣርቶ መከፈል ያለበትን ሂሳብ ለሚመለከተው አካል እንዲከፍል፤ ሊከፈል የማይችል ከሆነ ደግሞ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ እናሳስባለን፡፡

### 3.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

1. በ5054 የሒሣብ መደብ የተያዘውን ተከፋይ ሂሣብ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በተደጋጋሚ የፈሰስ ተመላሹን እንዲለቅልን ተጠይቆ አልተለቀቀልንም፡፡ ስለሆነም ተከፋይ ሂሣቡ ብር 509,910.52 ከገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር በጠየቅነው መሠረት ተመላሽ ከተደረገልን ለታለመለት ዓላማ የምናውል መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን፡፡
2. በ5061 የሂሣብ መደብ የተያዘው የመያዣ ብር 14,529.26 ሂሣብ ግን ናዝሬት ለተገነባው የኤጀንሲው ህንጻ መያዣ ሲሆን፣ ተቋራጩ ገንዘቡን ሳይጠይቅ አድራሻው ስለጠፋ ያልተከፈለ ሲሆን የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ኤጀንሲ በ2008 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝት ላይ መልስ ሰጥተውበታል፡፡

### 3.1.5. የኦዲተሩ አስተያየት

- ከኢጋር ድርጅቱ በዕርዳታ የተገኘውን ገንዘብ ለታለመለት ዓላማ መዋል ይኖርበታል፡፡ ለታለመለት ዓላማ የማይውል ከሆነ ግን ተከፋይ ሂሳቡ ወደ ገቢ እንዲቀየር፣
- የመያዣ ሂሳቡም እንዲከፈል አስፈላጊው ጥረት ሁሉ ተደርጎ ሊከፈል የማይችል ከሆነ ወደ ገቢ እንዲቀየር፣

ተደርጎ ተገቢው የሂሳብ ማስተካከያ እንዲሰራላቸው መደረግ እንዳለበት ልናሳስብ እንወዳለን፡፡

## 4. የወጪ ሂሳብ

### 4.1. የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ የተመዘገበ የድጎማ ሂሳብ፤

#### 4.1.1. ግኝት

በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ለወጪ ሒሳቦች ተገቢው የወጪ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ለአበባ አምራች ድርጅቶች ከባህርዳር ወደ አዲስ አበባ በየብስ ትራንስፖርት ለተጓጓዙ የኤክስፖርት ሆርቲካልቸር ምርቶች ለትራንስፖርት፣ የነዳጅ፣ የውሎ አበል፣ ቅባትና ዘይት ድጎማ ሲፈጸም ለብር 92,408.47 የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 1 ተያይዟል)

#### 4.1.2. ሥጋት

ለክፍያው ተገቢ የሆነ ማስረጃ የማይቀርብለት ከሆነ፡-

- ☞ የተዘጋጀውን የሂሳብ መግለጫ ተዓማኒነት ሊያሣጣው ይችላል።
- ☞ ለመንግሥት ገንዘብ አላግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ይችላል።

#### 4.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ ለተመዘገበው ሂሳብ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብለት ማስረጃ የማይቀርብለት ከሆነ ግን ገንዘቡ ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል።

#### 4.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ የተመዘገበ ሂሣብ በፌደራል መንግሥት የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት ለወጪ ሂሣብ ተገቢው የወጪ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ አበባ አምራች ድርጅቶች ከባህርዳር ወደ አዲስ አበባ በየብስ ትራንስፖርት ለተጓጓዙት የኤክስፖርት ሆርቲካልቸር ምርቶች ለትራንስፖርት የነዳጅ የውሎ አበል ቅባትና ዘይት ድጎማ ሲፈፀም ለብር 92,408.47 የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለጣና ፍሎራ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የካቲት 28 ቀን 2010 ዓ.ም በደብዳቤ

ቁጥር 18/በ09/10/181 በተጻፈ ደብዳቤ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብላቸው ክፍያ የተፈፀመባቸውን ማስረጃ በአጭር ቀን እንዲያቀርቡ፤ ካላቀረቡ ግን አሁን ከሚከፈላቸው ክፍያ ላይ ቀንሰን እንደምናስቀር አሳውቀናል።

## 5. <u>ንብረት</u>

### 5.1 <u>የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ላይ የታዩ ክፍተቶች</u>፤

#### 5.1.1 <u>ግኝት</u>

የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የንብረት አስተዳደር በመንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሠረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. የማያገለግሉ የተለያዩ የቢሮ መገልገያዎች፤ የመኪና መለዋወጫዎች እና ከእርሻና ተፈጥሮ ሃብት የመጡ የተለያዩ የቢሮ መገልገያዎች ያለአገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤
2. አላቂ እቃዎች በእስቶክ ካርድ ወይም በመዝገብ በተሟላ ሁኔታ የማይመዘገቡ መሆኑ፤
3. ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ለሠራተኞቹ በሞዴል 22 ወጪ የተደረጉ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች (ላፕቶፕና ዲስክቶፕ ኮምፒተሮች) ወጪ ሲደረጉ የንብረቱ ወይም የዕቃው ሴሪያል ቁጥር ያልተሞላ መሆኑ፤
4. ስምንት ተሽከርካሪዎች ለረጅም ጊዜ ያለአገልግሎት የቆሙ መሆኑ፤ (ለዝርዝሩ አባሪ 2 ተያይዟል)

ታውቋል።

#### 5.1.2 <u>ሥጋት</u>

- ☞ መጠገን ያለባቸው ንብረቶች በወቅቱ ካልተጠገኑ መወገድ ያለባቸው ደግሞ ካልተወገዱ ለከፋ ብልሽት ሊዳረጉና ዋጋቸው ሊቀንስ ይችላል።
- ☞ ለንብረት ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ።

### 5.1.3 የማሻሻያ ሃሳብ

የንብረት አስተዳደሩ መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት እንዲፈጸም እንዲሁም ከላይ በተገለጹት ክፍተቶች ላይ ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ መደረግ ይኖርበታል።

### 5.1.4 የሥራ አመራሩ ምላሽ

1. ቀደም ሲል በነበሩት ሁለቱ ተቋማት የነበሩት ንብረቶችና ተሽከርካሪዎች ወደ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ወደ አንድ ከተጠቃለሉ በኋላ ንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ ተቋቁሞ የሚወገዱ ንብረቶችን የመለየት ስራ ተጠናቆ ለማስወገድ የገማች ኮሚቴ ተቋቁሞ ስራ ጀምሯል።

2. ቀደም ሲል የሰው ኃይል እጥረት በመኖሩ አላቂ ዕቃዎች በእስቶክ ካርድ ላይ ሳይመዘገቡ ቀርተዋል። በአሁኑ ሰዓት ግን የመዝገብ ፀሐፊ የተመደበ በመሆኑ የምዝገባው ስራ እየተከናወነ ይገኛል።

3. ቀደም ሲል የነበሩት ሰራተኛ ሴሪያል ቁጥር በሞዴል 22 ላይ ያልመዘገቡ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ያሉት ሰራተኛ ወጪዎችን በሙሉ እየመዘገቡ የሚገኙ በመሆኑ ችግሩ እየተቀረፈ በመሄድ ላይ ይገኛል።

4. ለረጅም ጊዜ የቆሙ ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በሰጠው አቅጣጫ መሰረት ጋራዦችን በማወዳደር ያሸነፈው ተለይቶ የሥራ ውል በመዋዋል ወደ ሥራ ለመግባት እንቅስቃሴ ተጀምሯል።

## 6. ልዩ ልዩ

### 6.1. በሰነድ አያያዝ ላይ የታዩ ክፍተቶች፤

#### 6.1.1. ግኝት

የባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የሰነድ አያያዝና አመዘጋገብ የተደራጀ እና በቀላሉ ለመለየት እና ለማግኘት በሚያስችል መልኩ መደራጀቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፦

1. የወጪ ማዘዣ ደረሰኞች (PV) እና የምዝገባ ማዘዣ ደረሰኞች (JV) ተለያይተውና ተደራጅተው በቁጥር ቅደም ተከተል ያልተቀመጡ መሆኑ፤
2. አልፎ አልፎ የገቢ ደረሰኞች (RV) እና ወጪዎች የተወራረዱባቸው የምዝገባ ማዘዣዎች (JV) ከጥራዙ ላይ ተቀደው ከደጋፊ ሰነዶቹ ጋር ያልተያያዘ መሆኑ፤

ታውቋል።

**6.1.2. *ሥጋት***

- ☞ ሰነዶችን በቀላሉ ለማግኘት ሊያስቸግር ይችላል።
- ☞ ለሰነዶች መጥፋት ምክንያት ሊሆን ይችላል።

**6.1.3. *የማሻሻያ ሃሳብ***

ሰነዶች በአይነታቸው ተለይተውና በቀላሉ ሊገኙ በሚችሉበት አግባብ ተደራጅተው መቀመጥ ይኖርባቸዋል።

**6.1.4. *የሥራ አመራሩ ምላሽ***

የወጪ ማዘዣ ደረሰኝ (PV) እና የምዝገባ ማዘዣ ደረሰኝ (JV) የተደራጁበት ሁኔታ ሲታይ እንዳንዶቹ ያልተቀመጡበት ሁኔታ ይታይ የነበረው ምክንያት ሁለቱ መሥሪያ ቤቶች ከተዋሃዱ በኋላ ከነበርንበት መሥሪያ ቤት ወደ አዲሱ ህንጻ ስንመጣ በተለያዩ ካርቶን፣ እንደመጡ ተደርድረው ያላለቁበት ሁኔታ ነበር። ምክንያቱም የሰው ኃይል ችግር ነው። ከሰነዱ መብዛት የተነሳ ለመለየት እና ለማስቀመጥ ጊዜ እጥተን ነበር። አሁን ግን ሠራተኛ በመመደብ እያስተካከሉ ስለሚገኙ በአጭር ጊዜ አስተካክለን እናስቀምጣለን።

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት በባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ስለተደረገልን መልካም የሥራ ትብብር እናመሰግናለን።

አባሪ. 1

<u>የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ የተመዘገበ የድጎማ ሂሳብ ዝርዝር፤</u>

| ተራ ቁጥር | የቫውቸር ቁጥር | ወጪው የተመዘገበበት ቀን | የሂሳብ መደብ | ገንዘቡ የተከፈለው | በወጪ የተመዘገበው | የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ብር | ብር |
| **1.** | 433008 | 30/10/2009 | 6412 | የኢትዮ አግሪሴፍት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር | 594,254.28 | 29,503.13 |
| **2.** | 433007 | 30/10/2009 | 6412 | ለጣና ፍሎራ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር | 1,467,161.25 | 62,905.34 |
| **ድምር** | | | | | | **92,408.47** |

አባሪ .2

<u>ለረጅም ጊዜ ያለአገልግሎት የቆሙ ተሽከርካሪዎች ዝርዝር፤</u>

| ተራ ቁጥር | የመኪናው ዓይነት | የተሽከርካሪው የታርጋ ቁጥር |
|---|---|---|
| **1.** | ላንድ ክሩዘር | 4 - 05806 |
| **2.** | ዲኤክስ / አውቶሞቢል | 4 - 00168 |
| **3.** | ፎርኬ/አውቶሞቢል | 4 - 04253 |
| **4.** | ኒሳን | 4 - 02894 |
| **5.** | ሀርድ ቶፕ | 4 - 16262 |
| **6.** | ኒሳን | 4 - 04087 |
| **7.** | ሚስትቡሺ ላንሰር | 4 - 17240 |
| **8.** | ሀርድ ቶፕ | 4 - 23127 |

**በሥራ አመራር ሪፖርት በተጠቀሱት የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርዓ-ግብር**

የኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤት ስም:- ____________________________

ኦዲት የተደረገው ሂሳብ በጀት ዓመት:- ____________________________

የተዘጋጀበት ቀን:- ___________________

| ተራ ቁጥር | የኦዲት ግኝቶች | የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች | እስከአሁን የተወሰዱ ማስተካከያ እርምጃዎች | ቀሪ ማሻሻያ ሃሳቦች ተግባራዊ የሚደረጉበት ጊዜ | ኃላፊነት የተሰጠው የሥራ ክፍል | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |
| | | | | | | |

<u>**ማሳሰቢያ**</u>:- ይህ መርዓ-ግብር እና የኦዲት ሪፖርቱ ለመ/ቤትዎ እንደደረሰ የተወሰዱ እርምጃዎች በአስቸኳይ ተሞልቶ በ7 ቀናት ውስጥ ለመ/ቤታችን ካልተመለሰ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በምናቀርበው ዓመታዊ ሪፖርት ውስጥ "ለኦዲት ሪፖርት ማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርዓ-ግብር መልስ ያልላኩ መሥሪያ ቤቶች" ዝርዝር ውስጥ እና እርምጃ አለመወሰዱ ተጠቅሶ ለምክር ቤቱ ሪፖርት የሚቀርብ መሆኑን እንገልፃለን።